# ነፍስ ይማር ብለናል



ሐይሌ የኔ ወንድም ፤አቤ ይሻልሀል ውይንስ አካሌ

ወይንስ እንደባዳ ልበልህ እገሌ

አብሮ አደግ ወንድሜ፤የብዙ ዓመት ጓዴ

ስጠራህ ደራሼ፤መካሪዬ ሆዴ

ዛሬ ምን ሆነሐል ፤ብጠራህ አትሰማ

እንቅልፍ ተጭኖሀል፤እንዲህ የሚስማማ?

ጨኸቱ ጨዋታው፤ቀልዱ ቁም ነገሩ

ፅጥ አለ ቤቱ፤ተዘጋብኝ በሩ።

ሰተት በሎ ገብቶ፤ሞት በቀዳዳ

ብቻህን አግኝቶ፤ሊያደርግህ ለማዳ።

ውስጥህን አድምቶ፤አጥንትህን ግጦ፤ስጋህንም በልቶ

ሲወስድህ በጠዋት፤ተደብቆ አድብቶ

ድረሱልኝ ስትል፤ታግለህ ልትጥልው

እንዲህ በጠዋቱ፤ተጠቃህ ምነው?

የአርማጮሁን ገደል፤የጭልጋን ቁልቁለት

የመተማን ሜዳ፤የጫቆን አቀበት

የአላፋ ጣቁሳን፤የአዳኝ አገር ጋራ

ሽንፋ ስልፈረደ፤የቋራን ተራራ

እንዳልጠቀጠከው፤እንዲያ በእግርህ

ምንነው ታዲያ ዛሬ

ወለል ካለው ሜዳ፤እግርህን የያዘህ?

ደምክን እንዳልመልስ ፤ገዳይህ ነፍስ የለው

በምኑ መሣሪያ ፤ሞትህን ልግደለው።

አባት የለው እናት

ውንድም የለው እህት

ተደብቶ ገብቶ ሁሉን የሚኀትት።

ገዳይክን ከስሼ፤ፍርድ ቤት አቅርቤ

የፍጥኝ አስሬ፤በዱላ ደብድቤ

ለዳኜ ነግሬ፤በደሌን በሙሉ

ፍረዱኝ ባልኳቸው፤ለተመልካች ሁሉ፡

ልጆችህ ሳያድጉ፤ገና በጠዋቱ

ቴዲ ሳይመረቅ፤ሳትቆም ከፊቱ

እንዲያ እየወደደህ፤እንዲያ እየናፈቀህ

ወዴት ትሄዳለህ፤ምን አይነት ጨካኝ ነህ?

ረጋ በል ሐይሌ፤ምን ያስቸኩልሀል

መመለሻ የለም፤ይህንን አውቀሀል?

ቅድስት ስትጠራህ፤አቤት አትላትም

ዳዲ ትልሀለች፤ጠርታ አትጠግብህም።

መንገደኛው ሐይሌ እንደዚህ ከቸኮልክ፤ከተጣደፍክማ

ገበየሁን ልታይ፤አበበንም ልታይ፤ ከሙታን ከተማ

ነፍስህ ወደ ገነት፤ሥጋህ ከመሬት

ከፃድቃን መደዳ እንዲያስቀምጣት

ነፍስ ይማር ብለን፤ዛሬ ሸኘናት

ከ ወርቁ ማርዬ ኅዳር 27 2005 ዓ.ም (DEC 6 2012)

ለ አቤ ሐይሌ መታሰቢያ